ጠብታ አዘዘለት። ጠብታውን ያለማቋረጥ ባደርግለትም እርሱን ግን «አናቴ! ጆሮዬን አመመኝ» ከማለት አልተቆጠበም። ሕመሙ እየጸናበት ሄዶ፥ የማቅለሽለሽና ትኵረት የማጣት ችግር አስከተለበት። መምህራኑም ይህንኑ ችግሩን ማስተዋላቸውን ነገሩኝ። በዚህ ሁኔታ ለሦስት ወራት ሲቆይ፤ ምን እንደማደርግለት በጣም ግራ ገባኝ።

መስከረም ማለቂያ ላይ፤ አንድ ሌሊት በጣም እያለቀሰ እስከ ንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ድረስ ቆየ። ጠዋት ወደ ዶ/ር ነቢል ጣቢት ዘንድ ወሰድነው። ዶክተሩ ለዓሥራ አም ስት ደቂቃ በደንብ ከመረመረው በኋላ፤ በሕፃኑ ጆሮ ውስጥ በደም የተለወሰ ብረት ነገር ይታየኛል አለኝ። ብረቱ የሚታይበት አካባቢ ዙሪያው ቆስሎ፥ ፈሳሽ እያመነጭ ወደ ታንቡሩ ተንጠባጥቦ ተጠራቅሟል።

ጆሮውን ምንም ዐይነት ፈሳሽ ነገር እንዳለስነካውና ጉንፋን ሊያስይዙ ከሚችሉ ነገሮ ችም አርቄ እንድጠብቀው አስጠነቀቀኝ። ምክንያቱም ከቁስሉ የሚመነጨውን ፈሳሽ ስለሚያ ባብሰውና ለከፋ ችግር ስለሚያጋልጠው ነው። ይህ ተፅዕኖ ከበዛበት ደግሞ፤ የጆሮው ታን ቡር ይታወክል። ቁስለቱን የሚቀንስና ሕመም የሚያስታግስ አራት መርፌና የሚጠጣ ጸረ ባክቴርያ መድኃኒት አዘዘለት።

ጆሮው ውስጥ የገባውን ባዕድ ነገር ለማውጣት፤ ሙሉ ማደንዘዣ ተወግቶ ቀዶ ሕክ ምና ማድረግ እንዳለበትም አሳሰበኝ። ብረት መሰል ነገሩ ለስላሳ ስለ ሆነና ስለሚያሙለጨ ልጭ፤ እንደ ሻካራ ነገር በቀላሉ አይያዝልንም። ስለዚህ ጸሎት ብታደርጉ ጥሩ ነው አለኝ። በቁስሉ ምክንያት የመስማት ችሎታው መቀነስ አለመቀነሱን ለማረጋገጥ ሌላ ምርመራ አደረገ።

የቀይ ደም ሴሉ የኦክስጂን መጠን አነስተኛ በመሆኑና ሰውነቱ ጥንካሬ ስለሌለው፤ የጸረ ባክቴርያውን መድኃኒት እንደታዘዘው በተከታታይ አልሰጠሁትም። ሐኪሙ አይቶት የተሻለ ውጤት ባለማግኘቱ ያንኑ መድኃኒት በድጋሚ አዘዘለት። አፋጣኝ ቀዶ ሕክምና ካልተደረገለ ትም ከመስማት እንደሚያግደው ስጋቱን ገለጸልኝ። ለሦስት ቀናት በተከታታይ መድኃኒቱን ወስዶ የሕመሙ ስቃይ ትንሽ ስለ ቀነሰለት ሽሮፑን መስጠት አቆምሁ። ቀዶ ሕክምናውም ስላስፈራኝ፤ በኣጥቢያችን ወደሚገኘው የአቡ ሰይፊንና የቅድስት ዴምያና ቤተ ክርስቲያን ሄጀ፤ እግዚአብሔር ልጀን ይፈውስልኝ ዘንድ ስሙን (ቁርሎስ) በወረቀት ጽፌ ከመንበሩ ላይ አኖርሁት።

ጆሮው ውስጥ ያለውን ብረት ነገር አቡ ሰይፊን እንዲያወጣለት፤ ቁርሎስና ታናሽ እኅቱ ክሪስቲና ሁሌም በኣንድነት ይጸልያሉ። በጎዳር ወር የአቡ ሰይፊን በዓለ ንግሥ በነበረ ጊዜ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት እናቴ ካደመጠች በኋላ፥ ወደ አቡ ሰይፊን የሌቶች አንድነት ገዳም ሄዳ፤ ጸሎት አድርሳ የጣማፍ ጌራኒን ቅዱስ ሥዕልና ቅዱስ ሥጋዉ ላይ የተቀመጠ እምነት (መል ካም መዓዛ ያለው ቅመም) አመጣችልኝ። ሥዕሉን በእጄ ይዤ «ጣማፍ ጌራኒ! ከአቡ ሰይፊን ጋር ያለሽን ወዳጅነትና እርሱም ጥያቄሽን ሁሉ እንደሚመልስልሽ አውቃለሁ። እባክሽ ቁርሎስ ጆሮ ውስጥ የገባውን ነገር ያለ ምንም ቀ.ሕ. እንዲወጣለት በጸሎትሽ አሳስቢ» ብዬ ጸለይሁ።

ለኡምና ጌራኒ ይህን ስጸልይ፤ በእርግጥ በልቤ አስብ የነበረው፤ ሐኪሙ ለቀዶ ሕክ ምና ቅድመ ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ፥ ከጆሮው ውስጥ አየሁት ያለውን ፈሳሽ (ሰም)

ለማውጣት በሚያደርገው ሙከራ፤ ብረቱም አብሮ በቀላሉ እንዲወጣለት ነበር። ይህን ሐሳቤን ለሐኪሙ ባማከርሁት ጊዜ፥ እንዲህ ዐይነት ዕድል የለም (አይታሰብም) ብሎኝ ነበር። ቁርሎስ ከትምህርት ቤት ሲመለስ፤ በእጄ የያዝሁትን ሥዕል ተመልክቶ፤ እናቴ! ይቺን ሴት አውቃታለሁ። በትምህርት ቤታችን ስለ እርሷ ታሪክ ይነግሩናል። አቡ ሰይፊንን በጣም እን ደምት ወደውም ነግረውናል አለኝ።

ማታ ሊተኛ ሲል፥ ሥዕሉን ከትራሱ ሥር አኖርሁለት። እኩለ ሌሊት ላይ፥ በጣም ስላመመው፤ ጩኸቱ ከዕንቅልፋችን ቀሰቀሰን። እኔም የጣማፍን ሥዕል ከትራሱ ሥር አድር ጌለት እንዴት ይጮኻል? ስል አሰብሁ። ጆሮውንና ዙሪያውን እናቴ ከገዳም ባመጣችልኝ እምነት አሻሽሁለትና «የአቡ ሰይፊንና የጣማፍ ጌራኒ ጸሎትና በረከት በኣንተ ላይ ይደር። ከኣሁን በኋላ ሕመም ሲሰማህ፤ ከመጮኽ ይልቅ ጣማፍ ጌራኒ እንድታስታግስልህ በጸሎት ጠይቃት አልሁት።

በነጋታው ቁርሎስ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ አልቻለም። እኔም ቀዶ ሕክምና ከማ ድረግ ሌላ አማራጭ እንደሌለው ተሰማኝ። ስለዚህ ከሰዓት በኋላ፥ አጣጥቤ ወደ ሐኪም ቤት ልወስደው ዝግጅት ጀመርሁ። ራሱን ላጥበው ስል፤ ውጎ ጆሮው ውስጥ እንዳይገባ፥ የጣማፍ ጌራኒ ሥዕል ያለበትን ፎጣ አጣጥፌ፤ ጆሮውን ሸፍኖ አጥብቆ እንዲይዝበት ለቁርሎስ ሰጠ ሁት። ፎጣው ከእጁ አምልጦ ወደቀ። ከመሬት አንሥቼ ወደ ጆሮው ልመልሰው ስል፤ የጆ ሮው ጫፍ ላይ በሰም የተለወሰው ብረት ተንጠልጥሎ አየሁት። ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ ብረ ቱን ከጆሮው ላይ አነሣሁት። «ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን፤ ክብርና ምስጋና ለኣቡ ሰይፊን ይሁን፤ ክብርና ምስጋና ለጣማፍ ጌራኒ ይሁን» አልሁ። ይህ ተኣምር - ተኣምር - ተኣምር ነው! እያልሁ አለቀስሁ።

ይህንን ብረት ጆሮው ውስጥ የከተተው እርሱ ራሱ እንደ ሆነ ቁርሎስን ስጠይቀው፤ «አዎን! የዓሣ መጫወቻዬ (አሻንጉሊቴ) አፍ ውስጥ ተጣብቆ የነበረ ማግኔት ነው» አለኝ። የዓሣ መጫወቻውን ሰብሮ ማግኔቱን ከኣፉ ላይ ካላቀቀ በኋላ ነበር ወደ ጆሮው የጨመ ረው። ይህ ማግኔት ጆሮው ውስጥ ገብቶ ከመስከረም እስከ ታኅሣሥ ወር ድረስ ቆይቷል። የማግኔቱ መጠን የሰዓት ባትሪ የሚያክል ሲሆን፤ ጆሮው ውስጥ መክተቱን ለምን እንዳልነገረኝ ስጠይቀው፤ አወጣዋለሁ ብዬ በጆሮ መኮርኮርያ እየሞከርሁት ነበር አለኝ። እርሱ ለማውጣት ብሎ የተጠቀመው መላ ግን ማግኔቱን ይበልጥ ወደ ውስጥ ይገፋው ነበር። እኔም ለማስታገሻ ብዬ የማደርግበት ጠብታ ከብረቱ ጋር ምን ዐይነት ግጭት (reaction-ሪአክሽን) ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አያቅትም።

እናቴን በስልክ ጠርቼ ተኣምሩን ነገርኋት። ከዚያ ያዩት ዘንድ ወደ ሐኪም ቤት ስን ሄድ፤ ሐኪሙ የቁርሎስ ጉዳይኮ ምንም አዲስ ነገር አይኖረውም። ያላችሁ አማራጭ ቀዶ ሕክ ምናውን ማድረግ ብቻ ነው ሲል፥ ለማንኛውም ለውጥ ካለ አንድ ጊዜ ብቻ እይልኝ ብዬ ለመን ሁት። ባየው ጊዜ፥ የብረቱን ጆሮው ውስጥ አለመኖር ሲረዳ፤ እየተገረመ «የት አለ?» ብሎ ጮኸ። ከነፎጣው የያዝሁትን ማግኔት አሳየሁትና የሆነውን ሁሉ ነገርሁት።

«አቡ ሰይፊንና ጣማፍ ጌራኒ አወጡለት ማለት ነው?! አሁን ጆሮው ንጹሕና ምንም ቁስል የሌለው ነው። ከዚህ በኋላ ምንም ዐይነት ምርመራ አያሻውም። እውነተኛ ተኣምር

ተፈጽሞለታልና እንኳን ደስ ያላችሁ» አለን:: ዛሬ ወደዚህ ገዳም የመጣነው፤ እግዚአብሔር ስላደረገልን ታላቅ ሥራ፣ ስለ አቡ ሰይፊንና ጣማፍ ኄራኒ ጸሎት፣ ምልጃና ተራዳኢነት ለመመስከርና ለማመስገን ነው:: የእነርሱ ተራዳኢነት አልተለየንምና ልጄ ቄርሎስ ያለ ቀዶ ሕክምና መፍትሔ አግኝቷል::

(፶) <u>አዲስ ሕይወት ነው የተሰጠሽ</u>፦ ወ/ሮ ኤ.አር. ኅዳር ፲፬ ቀን ፳፻ ዓ.ም. በደብዳቤ የላከች ልን ምስክርነት:: በቅዱስ ሚናስ በዓለ ንግሥ ዋዜማ ለሚገባው ለጾመ ነቢያት (የገና ጾም)፥ ሁለት ቀናት ሲቀሩት ታመምሁ:: መንሥኤውም የደም ግፊቴ ከሚጠበቀው በታች በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው:: በማግስቱ ደግሞ የኩላሊት ምርመራ ቀጠሮ ነበረኝ:: ስለዚህ እንድታ ግዘኝ እናቴን ስልክ ደውዬ ጠራኋት::

እናቴ እኔጋ ለመድረስ ከሚወስድባት ጊዜ በላይ፤ ለሦስት ሰዓታት ዘገየችብኝ:: ምን ደርሶባት ይሆን? ብዬ ስለተጨነቅሁ አቡ ሰይፊንንና ጣማፍ ኄራኒን ጠርቼ፤ በሰላም ወደ ቤቴ እንዲያመጧት ጸለይሁ:: የማየት ችሎታዋ በጣም ደካማ በመሆኑ፥ በመነፅር እርዳታ እንኳን በደንብ አጥርታ አታይም:: በመጨረሻ ከአንዲት ሴት ጋር መጣች:: በመንገድ ላይ የነበረ ሕዝብ ሁሉ የዓይን ምስክር የሆነበት ተአምር መፈጸሙንም ነገረችኝ::

እናቴ መንገድ እያቋረጠች ሳለ፥ በአል-ሶዋኽ ድልድይ ላይ እየፈጠነች ስትሻገር መኪና ገጫት:: ከመኪናው ሥር ስትወድቅ የሞተች መስሏት ነበር:: እርሷ ብቻ ሳትሆን፥ በቦታው የነበረው ሕዝብና አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ ጭምር እንዳለቀላት ወስነዋል:: አሽከርካሪውም ከድንጋጤው ብዛት የተነሣ በጣም ይጮኽ ነበር::

ሕዝቡ ሁሉ ከመኪናው ሥር የተጋደመውን የኣረጋዊቷን አስክሬን ለማየት ተሰበ ሰበ:: እዚያው እንዳሉ፥ በሁለት ጎኖቹ ሁለት የወርቅ ሰይፎች የያዘ ሥርዓት አስከባሪ በፈረስ እየጋለበ መጥቶ፤ አጠገባቸው ቆመ:: አንገቱ ላይ የወርቅ መስቀል ያለው ሲሆን፤ ፈረሱ ላይ ከኋላው አንዲት ሴት ተቀምጣለች:: ጥቁር ቀሚስና ዐይነ ርግብ ለብሳ ነጭ መስቀል አንገቷ ላይ አጥልቃለች:: ሥርዓት አስጠባቂው ወደ መካከላቸው ገብቶ፤ እባካችሁ አትክበቧት፥ ምንም አልሆነችም አላቸው:: እናቴን ከመኪናው ሥር ሲያወጣት፤ ሴትየዋ (መነኩሲቷ ብለው ይሻላል) ደግሞ ቦርሳዋን ይዛላት ነበር:: ፖሊሱ (እኔ አቡ ሰይፊን ነው ብዬ አስባለሁ) የእናቴን ልብስ እያስተካከለ ወደ አእምሮዋ እንድትመለስ የመጀመሪያ እርዳታ አደረገላት::

የመኪናውን አሽከርካሪ፥ በጥንቃቄ ልታሽከረክር ይገባህ ነበር፤ ብሎ ሲገስጸው ሁሉም ሰምተዋል:: ምን ያስቸኩልሃል? በችኮላ ምክንያት የሆነውን አየህ አይደል? አሁን ወደ ጣቢያ ልውሰድህና ስለ አደጋው ላመልክትብህ? ሲለው፥ አሽከርካሪው በመርበትበት እያለቀሰ ይቅርታ ጠየቀው:: ጌታዬ ሴትየዋም እኮ እየሮጠች ስለ ነበረ ነው ያደናገጠችኝ፤ ምንም አማ ራጭ አልነበረኝም:: ግንኮ ደኅና ናት:: የተቧጨረ ነገር እንኳን በኣካሏ ላይ የለም አለው::

ጉዳት ደርሶባት ቢሆንማ ቀጥታ ወደ ጣቢያ እንደምወስድህ ታውቃለህ:: ለሁለተኛው ተጠንቅቀህ አሽከርክር:: አሁን መሄድ ትችላለህ አለው:: በቦታው የነበረው ሕዝብ ሁሉ እን ዲህ ዐይነት ፖሊስ አይተን አናውቅም ይባባሉ ነበር::

እናቴ ደግሞ፥ «በመንቃት ላይ ሳለሁ፤ ልሙት ተወኝ ለምን ትቀስቅሰኛለህ?» እያል ሁት ነበር:: እርሱም «እንዴት ነው አሁን ልሙት የምትዩው? የምታስታምሚው ሰው (እኔን ማለቱ ነው) ይጠብቅሻልኮ:: በይ ተነሽ በፍጹም አሁን አትሞቺም!» አለኝ ብላ ነገረ ችኝ:: ከነቃች በኋላ፥ ዙርያዋን የከበቧት ሁሉ፤ «ይህ ፖሊስና አብራው ያለችው ሴት፤ ከመ ኪናው ሥር ሲያወጡሽ፤ አዲስ ሕይወት ነው የተሰጠሽ» እያሏት ነበር::

ከመንገደኞቹ አንዱ፥ «ዘመዶችሽ ናቸውን? . . . አንቺን ሲያዩሽ ድሃና ጎስቋላ ትመስያለሽ:: እንዲህ ዐይነት የከበረ ሥርዓት አስከባሪ እንዴት ልታውቂ ቻልሽ? . . . ያቺ ከኋላው የጫናት ሴትስ? አንቺን ካዳኑሽ በኋላ ከነፈረሱ ተሠወሩ:: በእውነት አንቺ ደግ ሴት ነሽ:: . . . በተከሰተው አደጋ ሁላችንም ተደናግጠን ነበር» አላት::

እናቴን ይዛት የመጣችው ሴት፤ ቤት እስኪደርሱ ድረስ እየደገፈቻትና እየተንከባከ በቻት ነበር:: እናቴም በዚህ ዐይነት ተአምር መዳኗ ከአእምሮዋ በላይ ሆኖባታል:: ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀው ደግሞ፥ አቡ ሰይፊንና ጣማፍ በአደባባይ ተአምሩን መፈጸማቸው ነው:: ዐይኖቹን ከእኛ የማያነሣና ቅዱሳኑንም ይራዱን ዘንድ የሚልክ፤ ሳንጠራውም ቢሆን የሚደርስልን ልዑል እግዚአብሔር ከቅዱሳን ወዳጆቹ ጋር በአንድነት ከምስጋናዎች ሁሉ በላይ የሆነ ምስጋና ይገባዋል:: ለዘለዓለሙ አሜን::

(፶፩) <u>ሞቼ ነበር፤ በጣማፍ ኄራኒ ጸሎት እግዚአብሔር አስነሣኝ</u>፦ የወ/ት (ዋይ) እናት የመ ሰከረችው ነው:: እግዚአብሔር ሆይ! ኀይልህ ታላቅ ነው:: በቅዱሳንህ አድረህ የምታሳየው ኀይልም ታላቅ ነው:: ጣማፍ ኄራኒ ከጥልቁ ጉድጓድ አውጥታ ነፍሳችንን አዳነችልን:: ከደረ ሰብን ጉዳትና ከከበበን ጨለማ በሰማያዊው ብርሃን ታደገችን:: የእግዚአብሔር ብርሃን በእኛ በመገለጡ ሰይጣን አፈረ፤ ኀይሉም ደከመ:: እግዚአብሔር በምሕረቱ ጎብኝቶ ልጃችንን (ዋይ.ኤን.ኤፍ) እንዴት እንደታደገልን ለመመስከር ወደዚህ መጥተናል:: ለእኔም ለቤተሰቤም ለወዳጆቼም እርሷን በዚህ ሁኔታ ማግኘታችን ታላቅ ደስታችን ነው::

እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ተራዳኢነትና በጣማፍ ኄራኒ የጸሎት ኀይል ቸርነቱን እስካ ደረገልን ጊዜ ድረስ፤ ለአምስት ዓመታት ያየነውን እውነተኛ መከራና የእግዚአብሔርን የቸር ነት ሥራ ቅዱስ ስሙን በማመስገን እመሰክራለሁ:: ችግሩ የጀመረው የሁለት ዓመት ተኩል ዕድሜ ያላት ሕፃን ልጀ ወድቃብኝ መሬቱ ጭንቅላቷን በኃይል ሲመታት ነው:: በዚህ ምክን ያት የራስ ቅሏ ክፉኛ ተሰንጥቋል:: የሕክምና ባለሙያዎች የሰጡኝ አስተያየት፤ ሕፃን እንደ መሆኗ መጠን፤ ስንጥቁ ቶሎ ስለሚገጥም በፋሻ መጠቅለል በቂ ነው የሚል ነበር::

እኔ ግን፥ ሁኔታው ስላሳሰበኝ ወደ አቡ ሰይፊን የሴቶች አንድነት ገዳም ሄጀ ጣማፍ ኄራኒን፤ ወደፊት የሚፈጠረው ችግር አሰቃቂ ነውና ጸልዩላት አልኋት:: እዝን ባለ ሁኔታ ተመለከተችኝና «በሚቀጥለው ጊዜ ስትመጪ ልጅሽንም ይዘሻት ነይና እጸልይላታለሁ» አለ ችኝ:: የሦስት ልጆች እናት እንደ መሆኔ፤ በጊዜ እጦት ምክንያት ወዲያው ተመልሼ ለመ ሄድ (ልጀን ይገፍ) አልቻልሁም:: ጊዜው እየረዘመ ሲሄድ ደግሞ፥ ጭራሽ የነገረችኝን ረሳ ሁት:: በሌላ ጊዜ ሳገኛት «"ዋይን" እንድጸልይላት ለምን አላመጣሻትም?» ብላ ጠየቀችኝ:: የልጀን ስምና ችግሯንም ባለመርሳቷ እያስገረመችኝ፥ ጣማፍ አንድ ቀን ይዣት እመጣለሁ አልኋት:: አመጣታለሁ ብዬ ቃል ብገባም አሁንም ይዣት አልሄድሁም:: ስለዚህ ጣማፍ

ጌራኒ በዓፀደ ሥጋ ሳለች፣ ከልጇ ጋር ለመገናኘት ዕድሉ እያለ ሳላገናኛቸው ቀረሁ።

«ዋይ» የነበራት ሁኔታ ጤነኛ ስለሚመስል፣ የጭንቅላቷ ችግር በዚሁ ያበቃ መስሎኝ ነበር። በትምህርቷም በየደረጃው ጥሩ ውጤት ታመጣለች። እንደ ክርስቲያን ቤተሰብነታችን በእጥቢያችን በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን እየሄድን ትምህርት እንማራለን፣ አስቀድሰን እንቁርባ ለን። በቤታችንም የቅዱሳኑ ሥዕለ አድኅኖ ሙሉ ነው። የዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ስትሆን ግን፣ ልጄ ትምህርቷን መከታተልና ማጥናት የማትችልበት ሁኔታ ተፈጠረ። ጠባ ይዋ ሁሉ ተቀያየረና፣ የጀመረችውን ትምህርት በብዙ መከራ ለመጨረስ ብዙ ዓመት ፈጀባት። ለዚያውም አጥጋቢ ባልሆነ ውጤት።

ከጊዜያት በኋላ ደግሞ፥ ማታ ፅንቅልፍ መተኛት ተሳናት። ስለዚህ መብራት አብር ታና አልጋዋ ላይ ተቀምጣ ታነጋ ጀመር። ቀጠለችና ያልተጠበቁ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ፣ መጮኽና መረበሽ ጀመረች። ብዙ ጊዜም ራሷን ስታ ትወድቃለች። ወደ ብዙ ገዳማት ወስደ ናት ቀሳውስትና መነኮሳት እንዲጸልዩላት አደረግን። ቢሆንም ግን፥ ለጥቂት ጊዜ ፋታ ይሰጣ ትና እንደገና ይነግባታል። ካደገች በኋላ ስላለው ሁኔታ በራሷ ዐንደበት እንደሚከተለው ትመሰክራለች፦

«ዋይ»፦ ሰይጣን መፈተን ሊጀምረኝ ዕድሜዬ በሃያዎቹ አጋማሽ ላይ ነበር። ርኵስ መንፈስ ሕይወቴን በሙሉ ተቆጣጥሮ፣ የበሽታ ዐይነት አሸክሞ፣ ለቀዶ ሕክምና ቢዳርገኝም፥ ለችግሬ ግን ሳይንሳዊ መገለጫ አልነበረውም። ቅዠትም ስለሚያስቸግረኝ መንፈሴ ይረበሽ ነበር። በየ ገዳሙ እየሄድሁ የቅዱሳኑን ተራዳኢነት እማጸን ነበር። አምላኬ እግዚአብሔርንም በሥራዬ ቦታ በጓደኞቼ መካከል ሳለሁ የሚከሰትብኝን መንቀዥቀዥና ረብሻ እንዲያስቆምልኝ እጸልያ ለሁ። በዚህ ዐይነት ሁኔታ ለአምስት ድፍን ዓመታት ቆይቻለሁ።

በእኔ የደረሰውን መከራና ቤተሰቤም በእኔ ምክንያት ያሳለፈውን ፈተና፣ በቃላት ለመግለጽ ይከብደኛል። ለወላጆቼ ሴት ልጅ እኔ ብቻ በመሆኔ፣ እግዚአብሔር ደስታቸውን እንዲመልስላቸው ሁሌ እለምነዋለሁ። ቤተሰቤም እንዲሁ ያለማቋረጥ ይጸልዩልኛል። ወደ አቡ ሰይፈን የሴቶች አንድነት ገዳም መሄድ ባዘወትርም፥ ጣማፍ ኄራኒን ግን አግኝቻት አላ ውቅም ነበር። ዕረፍቷን ስሰማ የጸሎቷን በረከት እንደተነፈግሁ ስለተሰማኝ በጣም አዘንሁ።

እንዲጸልዩልኝ ከምጠይቃቸው ካህናት አንዱ፥ ሊቀ ካህናት አቡነ የሸብራ ቅዱስ ሚናስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው። እግዚአብሔር በበረከቱ ጎብኝቶኝ እስከተፈወስሁበት ጊዜ ድረስ፣ ይጸልይልኝ፣ ይመክረኝና ያጽናናኝ ነበር። እናቴም ከባድ የሥነ አእምሮ ችግር የደረሰ ባት ጊዜ በመሆኑ፣ ሰዎችን ከሴት ልጃቸው ጋር ካየች አምርራ ታሰቅሳለች፣ ሰው እንዲያና ግራት አትፈልግም። እግዚአብሔርንም አብዝታ ትወቅስ ነበር። አንድ ዐርብ ዕለት፥ ጥቅምት ፭፰ ቀን ፭፻፻ ዓ.ም. ግን ወደ አቡ ሰይፈን የሴቶች አንድነት ገዳም ጸሎት ለማድረስ ሄደች።

እኔም ምንም እንኳን ብዙ በሽታዎችን እያስተናገድሁ ቢሆንም፣ የጸመ ነቢያትን (፵ ቀናት) በሱባኤ ለማሳለፍ ወሰንሁ። ሰይጣን በዚህ ይበልጥ ሊፈትነኝ እንደሚፈልግ አውቃለሁ፣ ያም ሆነ ይህ ግን ለመጾም ቆርጬ ተነሣሁ። አንድ ቀን በሥራ ላይ ሳለሁ፥ ድንገት ሕመምና ድካም ተሰምቶኝ፣ እንደ እብደት ካደረገኝ በኋላ ራሴን ሳትሁ። ወደ ሐኪም

ቤት ተወሰጀ ብዙ የምርመራ ዐይነት ተደረገልኝ። አሁንም ቢሆን ግን፥ ሐኪሙ ለሕመሜ ምንም ዐይነት ሳይንሳዊ ስምና ምክንያት ሊሰጠው አልቻለም።

ወደ አእምሮዬ ስመለስ፣ ራሴን በመጥፎ ሁኔታ ላይ አገኘሁት። ሐኪም ቤት መቆየት ቢጠበቅብኝም፣ ወላጆቼ ኀላፊነቱን እኛ እንወስዳለን ብለው ፈርመው አወጡኝ። ወደ ቤት ከተ መለስሁ በኋላ ለመተኛት አልቻልሁም። ከአጋንንት ጋር ስታገል አደርሁ። የቅዱሳኑንና ሁሌም የማትተወኝን የእመ ብርሃንን ምልጃም እማጸን ነበር። በነጋታው ወደ አባ አቡነ ዘንድ ወስ ደው አስጸለየልኝ። እርሱና አብሮት የነበረ ዲያቆን ምን ያህል እንደደከምሁ አስተውለዋል። ቁሱም ምንም እንኳን የሰማንያ ዓመት አረጋዊ ቢሆንም፣ እየሰገደ ይጸልይልኝ ነበር።

ርኵስ መንፈሱ ወዲያው መሬት ላይ ጣለኝና፥ በኃይል እየጮኸ ይለፈልፍ ጀመር። ልፍለፋውን ካህናቱና በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ሁሉ ሰምተዋል፣ ቁሱንም ይዘልፈው ነበር። አንተ ማነህ? ወገንህስ ከየት ነው? ሲባል፣ አራት ነበሩና፥ ጥንት ወደ ጥልቁ ከወደቁት መና ፍስት ወገን የሆንን ሌጌዎን ነን አለ። በሰው ልጅ ላይ የምታደርሰው መከራ አይጸጽትህ ምን? ሲባል፥ ንስሐና ጸጸት ለእናንተ ለሰዎች ነው። እኛ የንስሐ ዕድል የለንም። ምኞትና ትዕቢት ከከበረ ሥፍራችን አንሥቶ አሁን ካለንበት ውርደት ጥሎናል። የሚውጠውን እንደ ሚፈልግ አንበሳ እያገሳን እንሮጣለን። የሰው ልጅ ግን፥ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የመመለስ ዕድል ተሰጥቶታል፣ ብሎ መለሰ።

ለልጅቷ የሚጸልዩላትና የሚማጸኑላት (ተራዳኢዎቿ) እነማን ናቸው? ተብሎ ሲጠ የቅ፣ ሰማዕታቱ የልዳው ቅዱስ ጊዮርጊስና የእስክንድርያው ቅዱስ ጊዮርጊስ[21]፣ አቡ ሰይፈን፣ ቅዱስ ሚናስ፣ ፖፕ ቄርሎስ ፮ኛ ሲል፣ ሌላስ? ዛሬ አብሯቸው የሚጸልይ ማነው? ተባለ። በጣም እየጮኸ፣ እዚያጋ የቆመችው፣ ሥዕሏ እዚያጋ ያለው . . . እያለ ከፊት ለፊት ግድግ ዳው ላይ ወዳለው የቅዱሳንን ሥዕለ አድኅኖ ወደያዘው የቀን መቍጠሪያ እያመለከተ። ንግ ሥቲቱ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያምም አብራት አለች አለ።

በልዑል እግዚአብሔር ስም ከእኔ እንዲወጣ ሲጠየቅ፣ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ጸሎት፥ በተለይ ደግሞ በጣማፍ ኄራኒ ጸሎት ምክንያት እንድለቃት አዞኛል እያለ ጮኸ። ይህ በሚሆን ጊዜ፥ እኔ አደርገው የነበረው የሰውነት እንቅስቃሴ፣ ማንም ሰው ላይ ታይቶ የማይታወቅ አስቀያሚ ጭፈራ ሲሆን፥ ሰውነቴ እንደ አባብ ይጥመለመል ነበር። መንፈሱም ኄራኒ በቃኝ . . . በቃኝ እያለ ይጮኻል።

ከዚህ በኋላ ጣማፍ ኄራኒ አባ አቡነክን አነጋገረችው። «መሬት ወድቃ ጭንቅላቷ መመታቱን ካወቅሁበት ጊዜ ጀምሮ እያለቀስሁ ነበር የምጸልይላት፣ ረስቻት አላውቅም። ነገር ግን በጸለይሁ ቍጥር፥ እግዚአብሔር «ፈተናውን ትቋቋመዋለች፣ በስቃይዋም ልክ ዋጋ ታገኝበታለች፣ ጊዜው ሲደርስ እኔ አጎበኛታለሁ፥ ይለኝ ነበር። አሁን ግን ይኸው ጊዜው ስለ ደረሰ እግዚአብሔር ርኵስ መንፈሱን ገስጾ አውጥቶላታል። ስለ ጊዜው መርዘም ራሷንም ሆነ እግዚአብሔርን እንዳታማርር ንገራት። መዘግየቱ በፈቃደ እግዚአብሔር ነውና» ብላ እንደ ነገረችው አባ አቡነክ ነግሮኛል። በእርግጥም ልክ ጣማፍ እንዳለችው ሁሉ፣ እናቴ በቂ

[21] የእነዚህ የሁለት ሰማዕታት ቅዱስ ዐፅም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ይኖራል።

ጥንቃቄ ብታደርግልኝ ኖሮ፤ . . . በጊዜ ወደ ጣማፍ ኄራኒ ወስዳ ብታስጸልይልኝ ኖሮ፤ . .
. በሽታዬ እንደዚህ አይብስብኝም ነበር፥ እያልሁ አማርርና አዝን ነበር::

አባ አኽኑክ ጣማፍን፥ ከመናፍስት ጋር በሚያደርገው ትግል ትረዳው ዘንድ ጠየ
ቃት:: እርሷም እንደምትረዳውና ለማንም ሰው ቢሆን የርኵስ መንፈስ ችግር ካለበት ዝም
ብላ እንደማታይ፣ አብዝታ እንደምትጸልይ ቃል ገባችለት:: አባ አኽኑክም በዚህ ዕለት ባገ
ኘው በረከት ተደስቶ እግዚአብሔርን አመሰገነ::

ርኵስ መንፈሱ ከእኔ ከመውጣቱ በፊት፥ ለሁለት ሰዓት ይለፈልፍ በነበረበት ጊዜ፤
ከቅጣቱ ኀያልነት የተነሣ፤ ተቃጠልሁ እያለ ሲጮኽ ለኣካባቢው ሰው ሁሉ ይሰማ ነበር::
እመ አምላክ፣ አቡ ሰይፊንና ጣማፍ የእርሱን ፈጽሞ መውጣት አጥብቀው ይከታተሉት
እንደ ነበርም ተናግሯል:: እኔም ሁሉም ርኵሳን መናፍስት ከለቀቁኝ በኋላ፥ ሰውነቴ መረጋ
ጋት ጀመረ:: ራሴን ሳውቅ በዙሪያዬ የከበቡኝ ሰዎች ሁሉ፤ ልክ ሞቶ እንደ ተነሣ ሰው ነበር
ደስ ብሏቸው እያቀፉ የሚስሙኝ::

ለእኔም የተሰማኝ፥ ለዘመናት አልጋ ላይ ተኝቼ ስማቅቅ እንደ ነበርሁና፤ እግዚአብ
ሔር በቅዱሳኑ፥ በተለይም ምን ጊዜም በማትለየኝ በእናቴ እመ ብርሃንና በጣማፍ ኄራኒ የጸ
ሎት ኀይል እንደ ረዳኝና ኀያል ፈውስን እንዳገኘሁ ነው:: ጣማፍ ኄራኒ ከዕረፍቷ በፊት
ጀምሮ በጸሎትና በዕንባ ታሳስብልኝ እንደ ነበር፤ ውለታዋን ምን ጊዜም አልረሳውም:: ዛሬ
ዐርብ ጥር ፩ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም. ከእናቴ ጋር ወደዚህ የመጣሁት ፈጣሪዬ እግዚአብሔርን፣
እመ ብርሃንን፣ ሰማዕቱ አቡ ሰይፊንንና ደጓ እናቴ ጣማፍን ለማመስገንና ተኣምሩንም ለመ
ናገር ነው:: ስማቸው እስከ ዘለዓለም ድረስ የተመሰገነ ይሁን፥ አሜን::

እንዲሁም በእኔ የሆነውን ሁሉ በጽሑፍ አስፍሬ አባ አኽኑክ ፈርሞበት አምጥቻ
ለሁ:: አንቺ ራስሽ ወስደሽ በእጅሽ ስጫቸው እንጂ በፖስታ ቤትም ሆነ በሰው እንዳትልኪ
ስላለኝ፥ በታዘዝሁት መሠረት ራሴ ይዤ መጥቻለሁ::

(፶፪) <u>አስቸጋሪ ከነበረው የባኽር ማዕበልና ወጀብ መካከል፤ ገባሬ ኵሉ የሆኑት የእግዚአብ
ሔር እጆች አወጡኝ</u>፦ ካፒቴን ነቢል ነቢሕ ሚካኤል፤ 3 ክሪስቶፊድስ መንገድ፤ ኤልሲዩፍ ባሕሪ ሰሜን
እስክንድርያ:: ነሓሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. መጥቶ የሰጠው የምስክርነት ቃል::

በዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን (እሑድ) ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ማታ በኣራት ሰዓት
ከሠላሳ ደቂቃ፥ በሥራ ላይ ነበርሁ:: በዚህ ምሽት ከእስክንድርያ የሚነሣውን መርከብ ከወ
ደቡ ለማውጣት አቅጣጫ የምመራው እኔ ነበርሁ:: የመርከቡ መጠን ርዝመቱ ሁለት መቶ
ሜትር፣ ከፍታው ከባሕር ወለል በላይ ዘጠኝ ሜትር፤ ወይም በሌላ አነጋገር፥ ባለ ሦስት
ፎቅ ሕንፃ የሚያህል ነው:: በዕለቱ የባሕሩ ሁኔታ አስቸጋሪ ነበር:: የማዕበሉ ከፍታ አራት
ሜትር ይሆናል:: መጠኑን ከላይ የጠቀስሁት ዐይነት መርከብ፤ በእንደዚህ ያለ ማዕበል ላይ
በኣየር እንደ ሚንሳፈፍ የዶሮ ላባ ሆኖ መጓዝ ማለት ነው::

መርከቡ ከእስክንድርያ ወደብ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቆ ከሄደ በኋላ፥ የሥራ ድርሻዬን
ስለተወጣሁ መርከቢቱን ለቀጣዩ ካፒቴን አስረከብሁ:: ከዚያ ከነበርንበት ርቀት ሆነን፥ ከተ

ማዋ የምትታየን ከመብራት እንደተሠራ ትንሽ አሻንጉሊት ሆና ነበር:: እኔ ከመርከቡ ወደብ
አጠገብ ቆሞ በሚጠብቀኝ ጀልባ ተሳፍሬ ወደ ከተማ ለመመለስ፤ ወደታችኛው የመርከብ
ክፍል በገመድ መሰላል እየወረድሁ ነኝ::

ገና ከገመድ መሰላሉ ወርጀ ሳልጨርስ፤ ካፒቴኑ በድንገት የመርከቢቱን አቅጣጫ
ቀየረው:: እኔ ገመዱን እንደ ያዝሁ፥ በኣየር ላይ ስወዛወዝ ማዕበሉ ደግሞ ገመዱን ከወዲያ
ወዲህ ያንገላታዋል:: በመርከቡ አቅጣጫ መቀየርና በማዕበሉ ምክንያት፥ ቆሞ በሚጠብቀኝ
ጀልባና በእኔ መካከል ትልቅ ክፍተት ተፈጠረ:: ርቀቱም በምንም መንገድ የማልደርስበት
ሆነ:: ኀይለኛ ማዕበል መጥቶ መሰላሉን ሲመታው ግራ እጅና እግሬ ተንሸራተው ቦታቸውን
ለቀቁ:: ወደ ባሕሩ ልወድቅና ልሰምጥ መሆኑን ሳስተውል «ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አቡ ሰይፊን፣
ጣማፍ ኄራኒ ድረሱልኝ ብዬ ጮኼ ተናገርሁ::

ወዲያው ደግሞ፥ «የገዛ ራሴ» ለራሴ ሁለት ሆኖ ታየኝ:: ራሴን ከርቀት ሆኖ በኣየር
ላይ ሲንሳፈፍ አየዋለሁ:: የመርከቢቱ ሙሉ አካል፣ የገመዱ መሰላልና ጀልባዋ ሁሉ ይታዩ
ኛል:: እንደገና ደግሞ፥ መሰላሉን በቀኝ እጀ ጨምድጀ ይዤ ተንሸራትቼ ከዘጠኝ ሜትር
ከፍታ ላይ ወደ ባሕሩ ስወድቅም ይታየኛል:: በዚህ ጊዜ ማዕበሉ እየጠበቀኝ የነበረውን ጀልባ
አንሥቶ እኔ ላይ ስለጣለው፤ በስተቀኝ በኩል የጎን ዐጥንቴ ተሰበረ::

ውኃው ላይ ካረፍሁ በኋላ፥ ሁለት መሆኔ ቀርቶ አንድ ራሴን ብቻ ይታየኝ ጀመር::
ከባድ ሕመምም ይሰማኛል:: ከመርከቢቱና ከጀልባዋ መካከል ባለው ቦታ ላይ፤ በማዕበል
ኀይል እየተገፋሁ ወደ ትልቅና ጨለማ ጕድጓድ ውስጥ እየገባሁ ነበር:: ከበላዬ ያለው ጀል
ባም ራሴን ይመታኛል:: ሰውነቴን እንደ ኳስ ጠቅልዬ፤ ከወዲያ ወዲህ እየተላጋሁ ነው::
ልክ ወፍጮ ውስጥ እንደገባሁ ሆኖ ተሰማኝ:: ለራሴም በጣም አዘንሁ::

ከፍርሓቴና ከጭንቀቴ የተነሣ፤ የማውቃቸውን ቅዱሳን ሁሉ እየጠራሁ ነበር::
ምንም እንኳን ባሕር ውስጥ ከጀልባ በታች ያለሁ ቢሆንም፤ ቅዱሳኑን ስጠራ ጨኸቴ ግልጽ
ሆኖ ለራሴ ይሰማኛል:: ጣማፍን ተጣርቼ «እናቴ! ድረሺልኝ» አልሁ:: ልቤንም ወደ እግዚ
አብሔር ለጸሎት አነሣሁ:: ከሰውነቴ ውስጥ እሳት የሚወጣ መስሎ ተሰማኝ:: ወዲያው
ጣማፍ ኄራኒን ውኃው ውስጥ አጠገቤ አየኋት:: እንዴት ሊሆን እንደቻለ ግን አላውቅም::

ፊቷን ሳየው በጣም አዝናለች:: አቡነ ዘበሰማያትን አብረን ደገምን:: ከዚያ ዳዊት ደገ
ምን:: «ዐይኖቼን ወደ ተራራዎች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረድኤቴ ሰማይና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚ
አብሔር ዘንድ ነው»፥ የሚለውን ጥቅስ ቃል በቃል እየተቀባበልንና ተራ በተራ እየተፈራረቅን
ደጋገምነው፥ መዝ.፻፳፡፩-፪:: «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝ የለም» የሚለውን ጸሎ
ትም ደገምን:: በውኃው ውስጥ አተነፋፈሴን ሳስተውለው፥ የባሕር ውስጥ ጠላቂዎች መተን
ፈሻ መሣሪያ፥ አፍና አፍንጫዬ ላይ የተገጠመልኝ ይመስላል:: ማዕበሉ ጀልባውን ባነዋወ
ጠው ቍጥር፥ የሚፈጠረው የውኃ መታወክ በጣም ጎድቶኛል::

ከጣማፍ ጋር መዝሙር ሀምሳን መድገም ጀመርን:: «. . . ከበደሌ ፈጽሞ አጠበኝ፥ ከኃጢ
ኣቴም አንጻኝ፤ . . .:: በሂጾጽ እርጨኝ እነጻማለሁ፤ አጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ:: . . .» ድምጿ
ጆሮዬ ላይ ያቃጭላል:: «እርሱ ይሰብራል፥ ዳግመኛም ይጠግናል፤ ይቀስፋል፥ እጆቹም ይፈውሳሉ» ኢዮብ

ፍ፡፲፰:: ከዚያ ደግሞ ድምጼን ከፍ አድርጌ «በመከራዬ ሳለሁ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፤ . . . እኔም፡ ከዓይንህ ፊት ተጣልሁ፤ ነገር ግን ወደ ቅዱስ መቅደስህ ደግሞ እመለከታለሁን? አልሁ:: . . .»፥ ዮናስ ፪፡፪፣፭:: ወደላይ ለመንሳፈፍ በማደርገው ሙከራ ሁሉ፥ ጀልባው ራሴን ይመታኛል:: በልቤም ጌታዬ ሆይ! ማሽኖቹን አቁማቸው» እያልሁ ነበር:: ጀልባው ከሥሩ ሁለት አክናፊ መዘውሮች አሉት:: እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ተሽከርካሪ ሰሃን መሰል ዝርግ መሣሪያ አላቸው:: የዙር ፍጥነታቸው አንድ ሺህ አምስት መቶ ዙር በደቂቃ (1,500 RPM) ነው::

ይህ መሣሪያ ካገኘኝ፤ እዚያው እንደ ሽንኩርት ከታትፎ ነው የሚጥለኝ:: ነገሩን ነው እንጂ፥ ከመሣሪያው ባመልጥም በነፍስ የመውጣት ተስፋ ያለኝ አልመሰለኝም:: ምክንያቱም አንድ የሰው ልጅ አሁን እኔ ባለሁበት ሁኔታ ባሕር ውስጥ ከወደቀ፤ እንደ ሞተ ይቈጠራል እንጂ ምንም ዐይነት የነፍስ አድን ሙከራ አይደረግለትም::

«ጌታዬ ሆይ! በመንግሥትህ ተቀበለኝ» እያልሁ እጸልያለሁ:: ከጣማፍ ኄራኒ ጋር አቡነ ዘበሰማያትን ጮኽ ባለ ድምፅ እየደገምሁ ቢሆንም፤ ሌሎችንም ቅዱሳን ሁሉ እየተ ጣራሁ ነበር:: በተለይ አቡ ሰይፊንን በጣም አብዝቼ ነበር የምጠራው:: ከዚያ ደግሞ እግዚ አብሔር ሆይ! ለቤተሰቤ ስትል ታደገኝ «የተስፋ ቢሶች ተስፋቸው አንተ ነህ:: . . . ረዳት ለሌላቸው ረዳታቸው አንተ ነህ:: . . . ለልበ ደካሞች ድጋፋቸው አንተ ነህ፤ ሰላም ትሰጣ ቸዋለህ . . . በማዕበል ላሉትም መጠለያቸው አንተ ነህ:: . . .» እላለሁ::

ባሕሩ ውስጡ በጣም ጨለማና አስፈሪ ቢሆንም፤ ሰውነቴ ሁሉ ቆሳስሎ ቢያመኝም፤ ውስጤን ግን ልዩ ሰላም ተሰማኝ:: ምንም በስቃይ ውስጥ ብሆንም ከሰማያት ግን መልስ እያገኘሁና የሚረዳኝ ሰው አብሮኝ እንዳለ ይሰማኝ ነበር:: ለዚህም ነው ልዩ መረጋጋት የተሰ ማኝ::...በድንገት ደግሞ ከጀልባዋ በሃምሳ ሜትር ርቀት፤ በኣስፈሪው ማዕበል ላይ እየተንሳ ፈፍሁ ነበር:: የጀልባው ሞተር ባይጠፋም፣ ማሽኑ ዙረቱን ባያቆምም፤ ከእኔ በሃምሳ ሜትር ርቋል:: ጨለማውና ማዕበሉ ግን አሁንም አስፈሪ ነው:: ውኃውን ጠጥቶ ከሚካበደው ልብሴ በተጨማሪ የተሰበሩ ዐጥንቶች ይዤ እንዴት መንሳፈፍ እንደ ቻልሁ አላውቅም:: ይህ ከእኔ አእምሮ መረዳት በላይ የሆነው የእግዚአብሔር እጅ መሆኑ አያጠያይቅም:: አንድ ጠብታ ውኃ አልዋጥሁም፤ አልሰመጥሁምም:: ስለዚህ የተሸከመኝ ሰው መኖር አለበት፥ ስል አሰብሁ::

ጀልባው ውስጥ ያሉት ሰዎች፤ ምን ዐይነት አሳዛኝ ነገር ነው? ሰውየው ሰጥሟል! ሲባባሉ ይሰማኛል:: በሕልም ዓለም፥ ወይስ በእውነተኛ ዓለም ውስጥ ነው ያለሁት? ሞቼ ይሆን? በሕይወት ልኑር? ምንም የማውቀው ነገር የለም:: ብቻ «ወደ አንተ እንጂ በድካሜ ወደ ማን እጠጋለሁ? ፤ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስትስ ሆይ! ልትታደገኝ የምትችል አንተ ብቻ ነህና በሰጊደ ልቡና ሆኜ ወደ አንተ እጸልያለሁ» ብዬ ከጸለይሁ በኋላ፥ ጀልባው ላይ ወዳሉት ሰዎች ተጣራሁ::

ገና ተጣርቼ ሳልጨርስ «ካፒቴን ነቢል! አይተንሃል:: ባለህበት ለመቆየት ሞክር፣ አትንቀሳቀስ አሉኝ:: እስከዚያች ደቂቃ ድረስ ያለ ችግር ተንሳፍፌ እንዳልነበር ሁሉ፤ ልክ የእነርሱ እጅ ሲነካኝ (የሰው ልጅ ሊታደገኝ በሞከረ ጊዜ)፥ መስመጥና ውኃውን መጠጣት ጀመርሁ:: የመታደግ ሙከራቸው ጭራሽ ስቃይ ሆነብኝ:: ለመጎተት ይረዳቸው ዘንድ የወረ

ወሩት ሽምቀቆ ገመድ ለወገቤ ሳይሆን ለኣንገቴ ተረፈ፤ ሲጎትቱት ተሽምቅቆ አነቀኝ:: በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነበርሁ:: ሆኖም ቅዱሳኑን መጣራቴን ቀጠልሁ::

ከደቂቃዎች በኋላ፥ የውኃ ላይ አምቡላንስ መጣልኝ:: ሕመሙ፣ ጭንቀቱ፣ ስቃዩ የምቋቋመው አልሆነም:: ኸሬይር በሚገኘው ገዳም በተደረገ አንድ ሰፊ ጉባኤ ላይ፥ ጣማፍ ኄራኒ የተናገረችው ቃል ትዝ አለኝ:: «መታመም መልካም (ጣፋጭ) ነው፣ በሽታ መልካም ነው፣ መፈወስም መልካም ነው» ፥ ነበር ያለችው:: እኔም ስለ አደጋው፣ ስለ ተቀበልሁት መከራ፣ ስለ ጭንቀቴ . . . ስለሆነው ሁሉ፤ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረብሁ::

ወደ ሆስፒታል ስወሰድ፥ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሆኗል:: እንደ ተነገረኝ ከሆነ፥ ባሕሩ ውስጥ ለሃያ ደቂቃዎች ቆይቻለሁ:: መላ አካሌ ስለ ቆሰለ፤ በተለይ ቀኝ ጎኔና ጀርባዬ ላይ ሕመሙ አስጨናቂ ነበር:: ሐኪሞቹ «ተስፋ የሌለው ሁኔታ ነው» ተባብለው ሲንሾካሾኩ ሰማኋቸው:: በዙሪያዬ ያሉት ሁሉ፥ ገጽታቸው በኃዘን የተዋጠ ነው:: እኔ ግን የሁሉ (የመከ ራዬም ጭምር) ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ማመስገን አላቋረጥሁም::

የራጅና የሌሎች ምርመራዎች ውጤት፥ የቀኝ ጎድን ስብራት፣ የጀርባ ዐጥንት መዛባ ትና የኣእምሮ መዛባት፣ ያልተስተካከለ የልብ ምት ወይም የኣተነፋፈስ መዛባት እና የውስጥ የደም ፍሰት ያሳያል:: በደም ፍሰት ምክንያት ሳንባዬ ተጎድቷል:: የራጂው ውጤት ላይ፥ ሳንባዬ እስከ ጭራሹ አይታይም:: በሕክምናው ተስፋ እንደሌለኝና ዕድሌ ሁሉ በእግዚአብ ሔር እጅ እንደ ሆነ፥ ለወንድሜ ነገሩት::

በሚቀጥለው ቀን ወደ ልዩ ማገገሚያ ክፍል ተወስጀ፤ ወደ አንጀቴ የሚደርስ ቱቦ በኣፌ በኩል ተከተተልኝ:: ፊቴ ላይ የኣየር መስጫ ከረጢት (ኦክስጂን ባግ) ተደረገ:: ሌሎ ችም ተጨማሪ የላስቲክ ቱቦዎችና ፈሳሽ ማስወገጃዎች በተለያየ የሰውነቴ ክፍል ላይ ተደ ረጉ:: በዚህ መካከል ጣማፍ ኄራኒ በሚያበራ ገጽ ተገልጣልኝ፤ «እግዚአብሔር ከዚያ አደጋ ያተረፈህ እዚህ መጥተህ እንድትተኛ ነውን? ቶሎ ትድናለህና ፍርሓት አይግባህ» አለችኝ::

ምንም እንኳን ሕመሙን ባልቋቋመውም፤ ደስታና ፍጹም ሰላም ተሰማኝ:: የእግዚ አብሔር እጆች ሥራቸውን ቀጥለዋል:: በነጋታው ከኣልጋዬ ላይ መነሣት እንዳለብኝ ከው ስጤ የሚቀሰቅሰኝ ነገር ነበር:: ያለ ማንም እርዳታ፥ ተነሥቼ ቁጭ አልሁ:: ይህ ፈጣን ለውጥ ለዶክተሮቹ የማይታመን ነበር:: የተጎዱት ዋና ዋና ቦታዎች ለውጥ በማሳየታቸው ድጋሚ ራጅ ተነሣሁ:: አሁንም ሐኪሞቹ ውጤቱን ማመን አልቻሉም:: ግማሽ ሊትር ደም ብቻ እንደ ቀዱ፤ ከጥቂት ቦታ በስተቀር ሳንባዬ በግልጽ ታየ:: አንጀቴም እንዲሁ መንቀሳቀስ አሳየ::

በማገገሚያው ክፍል ለስድስት ቀናት ቆየሁ:: እውነተኛው የነፍስና የሥጋ ዶክተር፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን፤ ቆይታዬ በደንብ ተረዳሁ:: ከዚህ በኋላ ወደ ማዕከላዊ አንደኛ ደረጃ ክፍል ተዛውሬ ለሃያ አምስት ቀናት ቆየሁ:: ምንም ዐይነት ቅዶ ሕክ ምና አልተደረገልኝም:: የሳንባዬ የቀኝ ክፍል ላይ ከሚታየው ጥቂት ዕብጠትና በትከሻዬ ላይ ካለው የመቧጨር ምልክት በስተቀር ሙሉ ጤነኛ ሆንሁ:: እነዚህ ሰውነቴ ላይ የቀሩት ትን ንሽ ምልክቶች፤ ጌታዬና መድኃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ «ከመከራ እንዴት እንዳተረፈኝ» ማስ ታወሻ ምልክቶቼ ናቸው:: ለዚህም እግዚአብሔርን እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ::

ካፒቴን ነቢል ሊመለከር ወደ ገዳማችን በመጣ ጊዜ፥ አንድ ሊቀ ካህናት አብሮት መጥቶ የሰጠው ምስክርነት፦ በቅስና ከመሾሜ በፊት፥ በባሕር ላይ ለሠላሳ አምስት ዓመታት አገልግያለሁ። እንዲህ ያለ ድንቅ ተአምር ግን አላየሁም። አንድ ጊዜ አንድ ጠላቂ ዋናተኛ፤ ከጀልባ ሥር ካለው እሽክርክሪት ጋር የተያያዘውን ገመድ እንዲፈታ ተጠይቆ ነበር። የታዘዘውን ከፈጸመ በኋላ፥ ወደ ላይ ሊወጣ ሲል የተሳሳተ እንቅስቃሴ በማድረጉ፥ ጀልባው ራሱን መታው። እርሱም ወዲያው ጸጥ አለ፤ አበቃ። ካፒቴን ነቢል ግን፥ በማዕበሉም፤ በገመዱም በጀልባውም ቢንገላታም፤ ስንት ጊዜ ቢቀጠቀጥም ተርፏል፤ ጤነኛም ነው። እግዚአብሔርንና የገዳማችንን ቅድስት እናት ጣማፍ ጌራኒን ከማመስገን ሌላ ምንም ቃል የለኝም። ልዩ የሆነው የጣማፍ ጌራኒ ፍቅር ካፒቴን ነቢልን ከሞት አፋፍ መልሶ፤ ክባኽር ሞገድና ከጨለማ አውጥቶ ለሰማያዊ ሕይወት አብቅቶታል። ጠማፍ፥ ልጆቹን ለአፍታ እንኳን የማይተወውን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅርም እንዲቀምስ አድርጋዋለች።

ውዷ እናታችን ጣማፍ ጌራኒ! ምስጋናችን ይድረስሽ።

«እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከሃገርህ፣ ከዘመዶችህም፣ ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን» ዘፍጥ.፲፪፥፩-፪። ከዘመነ አብርሃም በኋላም፥ እግዚአብሔር ለድንቅ ሥራው የሚመርጣቸው ልጆች፣ ወዳጆች፣ ሕዝቦች ነበሩት፣ አሉት። በመንፈሳዊ ጎዳና ላይ፤ እንደ ፀሓይ የሚያበሩ ዐምዶች፣ ልቡን ደስ የሚያሰኙት፣ በእነርሱ የልብ መሻቱን የሚፈጽምባቸው፣ የዕውቀት ጽዋ ያጠጣቸው፣ መለኮታዊ ብርሃኑን ያንፀባረቀባቸው፣ ጥሪውን ሰምተው ወደ እርሱ የሚፋጠኑና የሚተጉ በጎች፣ የእምነታቸውን ጽናትና ደግነታቸውን ተመልክቶ፤ የቃሉ መፈጸሚያ ያደረጋቸው፣ በግርማ ሞገሱ ያከበራቸው፣ ለትውልዱ ሁሉ የበረከት ምክንያት የሆኑ . . . ።

ውዷ እናታችን ጣማፍ ጌራኒም ከእነዚህ የእግዚአብሔር ምርጦች አንዷ የሆነች፣ በመንፈስ ቅዱስ እየተመራች ለታላቅ ክብር የበቃች፣ የጥበብን ጥሪት ለመቀበል ታማኝ ሆና የተገኘች፤ በትሕትናዋ፣ በበጎነትዋ፣ ራስዋን በመርሳት፥ ጸጋ እግዚአብሔርን ያገኘች ናት። የእርሷ ሕይወት የሆነው ሰማያዊ ተክል፥ ሥሮቹ ገዳሙን የከበቡት፣ ፍሬውን ገዳማውያኑ የሚመገቡት፣ ከምንጩ የሚጎነጩት፣ ለገዳማችን ኩራት፣ ሀብትና መመኪያ ነው። እርሷ ለገዳማችን፥ ቅጠሎቹ ሰፋፊ የሆኑና ባለ ብዙ ቅርንጫፍ የሆነ የዛፍ ግንድ ናት። እግዚአብሔር በእርሷ ያሳደረው መንፈሳዊ ፍሬ፥ ለእኛ ለመንፈስ ልጆችዋ ብቻ ሳይሆን፥ ለተሳላሚ ዎቹ ሁሉ ተርፏል።

ያያት፣ የተመለከታትና ያስተዋላት ሁሉ፤ ጠንካራ እምነትዋን ልብ ይላል፣ ይረዳ ልም። ከእርሷ አንደበት የወጣ ቃል ሁሉ፤ ወደ አድማጭ ልብ የመዝለቅ ኀይል አለው። ሃይማኖትን እንዲረዱና እንዲያዩ፣ ሰላምም እንዲያገኙ ያደርጋል። ከእርሷ ጋር የተነጋገረ ሁሉ ልቡናው በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ለምልሞ፣ ሰላም በውስጡ ሰፍኖ፣ ዓለሙን ንቆ ሰማያዊውን መንግሥት ናፍቆ ይመለሳል። በበዙ ወጣቶች ላይ ያመጣችውን የሕይወት ለውጥ በዓይናችን ተመልክተናል። ጎዳናቸው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የተመራ፣ የለመለመና ያበበ፣ በመልካም ምግባር የታጀበ ሆኗልና። እርሷን ያዩ ሁሉ፤ ገዳማዊነትን እንደ መልካምና ውብ አበባ እንዲያዩትና እንዲናፍቁት፣ ስመ እግዚአብሔርንም እንዲያመሰግኑ አስችላለች። ላያት ላደመጣት ሁሉ ምክንያተ ድኂን ሆናለች።

ውድ እናታችን! የገዳማችንና የምንኩስና ሕይወታችን ማስዋቢያ ውድ ዕንቊ ናት። ገና ከእኛ ጋር በምድር ላይ በነበረች ጊዜ፥ ከቅዱሳኑና ከግሑሳኑ ጋር አንድነት ነበራት። የሰማይ መላእክትም ተደስተውባታል። በፍቅረ እግዚአብሔር የተቃጠለው መንፈሳዊነቷ ምስጉን ነው። እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ መፈጸሚያ ያደረጋት እናታችን፤ ለቅድስና ስላደረገችው ተጋድሎ፥ ንዕድት፣ ብፅዕት፣ ቡርክት ናት።

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፤ በእናታችን ጣማፍ እውን መሆኑን አይተናል። እርሷ በሄደችበት ሁሉ፥ የበረከት ምንጭ፣ የድኅነት ጀልባ፣ የድኻ መጠጊያ ናት። የእርሷ ውለታ በምን ይመሰሰ ይሆን? ምንስ ዐይነት ቃል እርሷን ይገልጥ ይሆን? እርሷ፥ ውድ ዕንቊአችን፤ ታላቅ አማላጃችን፣ ለሁሉ የምታበራ የፍቅር ፋና፣ በንጽሕና የኖረች፣ እንደ ሻማ እየቀለጠች ለሌሎች ያበራች፣ ብዙ መቶዎችን ወደ ገዳማዊነት ያመጣች፥ የፍቅርና የትሕትና ምንጭ፣ ልምዷ በእምነት የጸና፣ የክርስትና ዓምድ፣ ሕይወቷ ብዙዎችን የማረከ፣ የኀላፊነትና የሕመም መከራ ሰላሟንና ፈገግታዋን ከፊትዋ ያላጠፋባት፣ የማኅበረ መነኮሳት አባት የሆነው፥ አባ ጳኩሚየስ ተጋድሎዋን ተመልክቶ፥ የአንድነት ችቦውን አብርቶ የሰጣት፣ በኃይለ እግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ስንቱን በሽተኛና ስንቱን ቁስለኛ ፈወሰች? በሥጋም በመንፈስም ስንቱን ታደገች?

ውድ እናታችን እማሆይ ጌራኒ! አንቺ ምን ዐይነት የፍቅርና የሰላም ሰው ነሽ? ንጹሕ ልብሽ በፍቅረ እግዚአብሔር የታጠረ በመሆኑ ወደ አንቺ የቀረበ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ቸርነት ያያል። አንቺን ያነጋገረ ሁሉ በተባረከ ጸሎትሽና ድጋፍሽ ሥር ይጠለላል። በሕይወት ዘመኑ በሚገጥመው መከራ ሁሉ በአንቺ ምልጃ ይተማመናል።

ውድ እናታችን እማሆይ ጌራኒ! በልዑል እግዚአብሔር አንደበት የተመሰገንሽ ናት። ለላብያተ ክርስቲያናት የማይረሳ ቅርስ ትታ አልፋለች። የምንኩስና ሕይወት፥ የቅዱሳን ሞገስና ክብር እንዲያድርበት አድርጋለች። በጠቅላላ ዕውቀትም፣ በመንፈሳዊው ዕውቀትም፣ በምሕንድስናው ዘርፍም፣ ለእኛ ለልጆቿ ብዙ ቅርሶችን አውርሳን አልፋለች። በሰማያዊው መንግሥት እስክንገናኝ ድረስ፤ ልዑል እግዚአብሔር (ወንዶችም ሴቶችም የመንፈስ ልጆቿን) በቤቱ ይጠብቀን ዘንድ በጸሎቷ ኀይል እንማልዳለን። ልክ በምድራዊ ሕይወቷ በነበረች ጊዜ ታደርገው እንደ ነበረው ሁሉ፤ አሁንም በገነት ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር፥ በጸሎት አብራን ትሆንና ታሳስብልን ዘንድ፣ በመካከላችንም ትገኝልንና ታተጋን ዘንድ የልብ ምኞታችን ነው። እርሷ በዚች ምድር ላይ ፈጣሪያችንን አስደስታ እንደኖረች ሁሉ፤ እኛንም እጆቻችንን ይዛ በዚሁ መንገድ ትምራን። ለዚህም የእመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያምና የሰማዕቱ አባታችን ፊሎፓተር መርቆሬዎስ (አቡ ሰይፊን) ምልጃና፤ የውድ አባታችን የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሳልሣይ ጸሎት አይለየን። ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሳልሣይ፥ እግዚአብሔር ረዥም ዕድሜና ጤና ይስጥልን![22] ለዘለዓለም አሜን።

ጥቅምት ፭ ቀን ፭፻፬ ዓ.ም.። /20 Babah 1728/ (30 oct. 2011)
የቅዱስ ዮሐንስ ሐዊርና፥ የጣማፍ ጌራኒ ዝክረ ዕረፍት።

[22] {ይህ መጽሓፍ የተዘጋጀው፥ ክብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ፫ኛ ዕረፍት በፊት ነው።}

ከጣማፍ ጌራኒ በኋላ የአመምኔት ምርጫ።

እናታችን ጣማፍ! ከሠላሳ አራት ዓመታት በፊት፣ በትንቢት መነፅር ተመልክታ እን ደተናገረችው ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዛሬው ዕለት ፲፩/፯/፳፻፩ ቃልዋ ዕውን ሆነ። ገና እማሆይ ኬርያ በወጣኒነት ስትመጣ ነበር፣ ይህች አዲስ ተክል አድጋ ብዙ ታፈራለች፣ የኣስ ተዳደሩን ችቦ ትቀበለኛለች ብላ ኡምና ጌራኒ የተናገረችው። በዛሬው ዕለት ዕድሜና ጤና ይስጥልንና፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኑዳ ፫ኛና፣ የቢሮ አባላቱ ብፁዓን አባ ዮሓንስና አባ ኤርምያስ፣ በኣንድነት መጥተው የትንቢቱን ፍጻሜ አሳዩን። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ፣ የያኔዋ እመምኔት እማሆይ ኬርያ ዋስፍና ሌሎ ችም እናቶች፣ ስለ ጣማፍ ጌራኒ እመምኔትነት በኣንድ ወቅት ተንብየው ነበር። ታሪክ ራሱን ይደግማል እንዲሉ፥ እርሷም ከብዙ ጸጋዎቿ አንዱ ሀብተ ትንቢት ነውና፣ እማሆይ ኬርያን በማንኛውም እንቅስቃሴዋ ሁሉ፣ ትከታተላትና ትመራት ነበር፣ ከእርሻዋ መልካም ተክሎች አንዷ ናትና። ይህ ቅርንጫፍ አንድ ቀን የማኅበሩ ግንድ ሆነ፥ ኀላፊነት ይሸከማል ብላ በየ ጊዜው ተናግራለች። ይህን ትንቢት ከነገረችን በኋላ ግን፥ ቀኑን በትዕግሥት ጠበቀች።

አንድ ቀን፥ ብጹዕ ወቅዱስ አባታችን፣ ከተለመደ አሠራሩ ለየት ባለ ሁኔታ፥ ቀጣይዋ እመምኔት ማን ትሁን? በሚል፥ ያለንን አስተያየት በወረቀት ጽፈን እንድንሰጠው ጠየቀን። የሁሉም ወረቀት የእማሆይ ኬርያን ስም የያዘ ሆነ። እርሱም ውጤቱን በታላቅ ደስታ ነበር ያሳወቀን። ለዚህ ምርጫ ምንም ዐይነት ቅድመ ዝግጅት አልተደረገም። እርሷም ብትሆን፥ በብዙዎች ዘንድ ብዙ ታዋቂ አልነበረችም። ሆኖም ግን፥ መንፈስ ቅዱስ በጊዜው የጣማፍ ኄራኒን ትንቢት እውን አደረገው። አቡነ ዮሓንስና አቡነ ኤርምያስም «ዛሬ የሆነው ፍጹም ግብረ መንፈስ ቅዱስ ነው» አሉ። በአስተዳደር ሹመት ተደርጎ የማያውቅ አዲስ ታሪክ ነውና፣ በቤተ ክርስቲያን ተዘግቦ ይቀመጣል። ጣማፍ ኄራኒ አልሞተችም። ሁሌም ከእኛ ጋር ናት። በግብፅ ብቻ ላሉት ሳይሆን፥ በዓለም ላይ ላሉት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሁሉ የጸሎቷ በረከት አይለየንም።

፳፱/፯/፳፻፩ እንዲሁ ለእኛ ልዩ ቀናችን ነበር። ሃያ ስድስት ወጣንያን የመነኰሱበት፣ በሥርዓቱ ላይም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኑዳ ፫ኛ፥ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አባ ሩዊስ፣ አባ ቡትሮስ፣ አባ ዮሓንስ፣ አባ ቄርሎስ አባ ሚና፣ አባ ኤርምያስ፣ አባ ዳንኤል እንዲሁም የተለ ያዩ የሴት ገዳማት እመምኔቶችና መነኰሳይያት፣ ለምሳሌ ጣማፍ ማርያም፣ እማሆይ ኤዱ ሮሲስ፣ ...የተገኙበት ነበርና። ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፥ የጤንነቱ ሁኔታ ሳያግደው፣ ጊዜው ንና ጉልበቱን መሥዋዕት አድርጎ፥ በታላቅ ክብር ነበር እናቶችን (እኅቶችን) ያመነኰሰልን። በዚሁ ዕለት፥ እማሆይ ኬርያ የአሮጌዋ ካይሮ አቡ ሰይፊን የሴቶች አንድነት ገዳም እመምኔት ሆና ተሾመች። በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ቀጥሎ ያለውን ቃለ ምዕዳን አደረጉ፡[23]

«የሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ የሴቶች አንድነት ገዳም አባላት በሙሉ! እማሆይ ኬርያ አዲስ እመምኔት ሆና ስለተሾመችላችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ። ከተወዳ

[23] {የሊቃነ ጳጳሳቱን ሀገረ ስብከታቸውና ገዳማቸውን ያልጠቀስሁት አስፈላጊ ሆኖ ስላልታየኝ ነው። ዋናው መጽ ሐፍ ላይ ግን የእያንዳንዱን ሊቃነ ጳጳሳት ሀገረ ስብከትና የሥራ ኀላፊነት እንዲሁም የመነኰሳይያቱን ገዳማ ትና አካባቢ ጠቅሰውታል። ስለዚህ መረጃው ከተፈለገ ዋናውን መጽሐፍ አግኝቶ ማየት ይቻላል።}

ጀኛ የተከበረች እናታችሁ እማሆይ ኬርያ ጋር በመንፈሳዊ አንድነት፣ በታዛዥነትና በፍቅር ትኖሩ ዘንድ አሳስባለሁ። በክርስቲያኖች ዘንድ ታላቅ ከበሬታ ያለውን ገዳማችሁን፣ በዚያው መሥመር ውስጥ ልታስሄዱት ይገባችኋል»። «እማሆይ ኬርያም እንዲሁ፥ እናንተ ልጆቿን በፍ ቅርና በትሕትና ታገለግላችሁና፣ በእርሷ የጎላፊነት ዘመን ደኅንነታችሁ ተጠብቆ ሰላማዊ ሕይ ወት ትኖሩ ዘንድ ምኞቴ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ጎይል አግኝታ፥ በጥበብ ትመራችሁ ዘንድ፣ የእናንተም ታዛዥነት ሥራዋን ያቀልላት ዘንድ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይሁን»።

<u>የጣማፍ ጌራኒ፥ ሁለተኛ ዓመት መታሰቢያ</u>

በሚዘከርበት ዕለት ብፁዕ አባ አርሳንዮስ የሜንያ መጢሮቦሊጥ፥ ያደረገው ቃለ ምዕዳን፦ በሰመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ! አሜን። ምንም እንኳን ስለ ጣማፍ ጌራኒ ብዙ ተጽፎ ብናነብም፣ ምንም እንኳን በምድራዊ ሕይወታ ያዩዋትና አብረዋት የነበሩ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ስላላት የጠበቀ ግንኙነት፣ አብዝተው ቢነግሩንም፥ በእርግጥ ከእኛ ጋር በነበረች ጊዜ ከኖረችው (ከፈጸመችው) ሕይወታ ጥቂት ጠብታ ብቻ ተነግሯል።

የኔታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት በጽኑ እምነት ተምራ ፈጽማዋለች፣ የሰማይ መላእክት ማረፊያ ሆና ተገኝታለች፣ ብዙዎችን ወደ ንስሐ መልሳለች። ወደ እርሷ የቀረበ ሁሉ፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል እንዳደረባት በቀላሉ ይረዳል። ገዳማዊውን ሕይወት ለከፍተኛ ደረጃ አብቅታለች። ይህ ሥራዋ፥ ብዙዎችን እንዲመነኵሱና የእርሷን ፈለግ እንዲከ ተሉ አድርጓቸዋል። ልቧ በፍቅር የተቃጠለ በመሆኑ፥ ያንን ሁሉ ሕመም ተቋቁማ፣ ለሥራ እንድትነሣ ያደረጋት ሰው ነች። የሥጋ ድካሟና ሕመሟ፥ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዋን ለመግ ታት አልተቻላቸውም። የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን ቃል ለእርሷ መጥቀስ ይቻላል። «የክርስ ቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደ በዛ እንዲሁ መጽናናታችንም ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናል» ፪ኛ ቆሮ.፩፥፭።

የኖረችበት ገዳምዋ እና በውስጡ ያለው እያንዳንዱ ሽርፍራፊ መሬት፣ ቡሩካን እጆ ችዋ የነኩት፣ እግሮችዋ ያረፉበት ቦታ ሁሉ ፍሬያማ የሆነውም ለዚህ ነው። በሥጋ ብትለየ ንም፥ በመንፈስ ከእኛ ጋር ናት። ፍቅሯ በእያንዳንዱ ባስተማረችን ትምህርት ውስጥ ታት ሟል። መነኰሳት እርስ በእርሳቸው ሲዋደዱ፣ ሲረዳዱ፣ እንግዳን በትሕትና ሲቀበሉ፣ የተቸ ገረ ሰውን ሲረዱ፣ . . . በዚህ ሁሉ ውስጥ የጣማፍ መልካም አርኣያነት አለ።

የቀደምት ደናግል በረኻውያት እናቶቻችንን ታሪክ እያጠናን ወደ ታች ስንወርድ፣ የእኛ ውድ እናት ከሆነችው ጣማፍ ዘንድ እንደርሳለን። የድንግልናና የሰማዕትነትን ክብር በምንኩ ስና ሕይወት ውስጥ የተጎናጸፈች፣ ሥራ ወዳድ፣ በጸምፅ በጸሎትና በስግደት ብቻ ሳይሆን፣ በም ግባረ ሠናይ ጥሙድ የሆነች፣ መከራን ለመቀበል የተዘጋጀች፣ የሁልጊዜ ናፍቆቷና ምኞቷ የገዳማትን ዕድገትና መስፋፋት ለማየት ብቻ የሆነ . . .፣ ክብርት የሆነች የክርስቶስ ሙሽራ ናትና። ይህን ከቀደምት አበውና እማት የተቀበለችውን መንፈሳዊ ትውፊት ለእኛ ለልጆቿም በማውረስ፣ የአበው ተጋድሎ በእኛም በርቶ እንዲታይ የተቻላትን ሁሉ አድርጋለች። የምንኩስና ሕይወት ጥንተ መሠረቱ እንዳይናድና ሥርዓት ዐልባ እንዳይሆን፥ ከታላ ላቆቿ ጋር በመማከር፣ እግዚአብሔርም ሥርዓቱን ይገልጥላት ዘንድ በጸምና በጸሎት እየተ ማጸነች፣ እርሱ በገለጸላት ብርሃን፥ ገዳማቱ ወደ ቀደመ ሥርዓታቸው እንዲመለሱ፣ በግን ባታ ሥራዎቹም ሆነ፣ በኣስተዳደራዊ ጉዳይ እንዲሁም፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በምታደርገው ድርድር ታላቅ ገድል ፈጽማለች።

እኛም ይህንን ታሪኳን በመጽሐፍ አሳትመን ለመጪው ትውልድ ስንተው፤ የእር
ሷን መንፈስ ያጠነከረና ልቧን ያጸና፣ አእምሮዋን ያነሣሣ የመንፈስ ቅዱስ እሳት በእኛም
አድሮ ተቀጣጥሎ ይነድ ዘንድ፣ የጸሎቷ በረከትም፥ የእርሷን ሕይወት በተመስጠ ባስተዋ
ለው ላይ ሁሉ ያድር ዘንድ ምኞታችን ነው። ይህ ምኞታችን የተሳካ ይሆን ዘንድ፤ ለሰው
ዘር ሁሉ አማላጅ የሆነችው፥ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን፤ የገዳማችን ጠባቂ
የባለ ሁለት ሰይፉ ቅዱስ መርቆሬዎስንና የእናት ጣማፍን ምልጃና ጸሎት እንጠይቃለን።

<u>ምስጋና ለኣብ፥ ምስጋና ለወልድ፥ ምስጋና ለመንፈስ ቅዱስ</u>፦ በቅዱሳን ወዳጆቹ አማካይነት
የቸርነት ሥራውን ይሠራልናልና፣ እጹብ ድንቅ ፍቅሩንም ይገልጽልናልና፥ ክብርና ምስጋና
ሁሌም ለእርሱ ይሁን። ከእነዚህ ቅዱሳን ከሆኑት ማደሪያዎቹም አንዷ፥ የገነት ዕንቊ የሆነ
ችው፣ በዚህ ዘመን የገዳማውያን ምሳሌ ሆና፥ የምንኩስናን ሕይወት ያበራችው ጣማፍ
ኄራኒ ናት። እርሷን እመምኔት አድርጎ የሰጠንን አምላካችንን እጅግ አድርገን እናመሰግና
ለን። በንጹሓን እጆቿ እየተንከባከበችና በጥዑም አንደበቷ እያስተማረች አሳድጋናለች። ከተቀ
ደሰ ሕይወቷ ውኃ ጠጥተን፥ ጥማችንን አርክተናል። ገዳማዊ አስተምህሮዋና መንፈሳዊ
ትጋቷ ለሕይወታችን ብርሃን ሆኖልናል። ለወዳጇ አቡ ሰይፊንም ለእርሷም በሰጊድ ሆነን
ምስጋናችንን እናቀርባለን። በሰማያት እስክናገኛት ድረስ እንደማትለየንም እናምናለን።

ለውድ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችንም ምስጋናችን እጅግ የላቀ ነው። በግብፅም በው
ጪም ስለምንገኝ፥ ስለ እኛ ስለ ቤተ ክርስቲያን ልጆች፣ ስለ መነኮሳቱና መነኮሳይያቱ
ሲል፣ እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን! አሜን።

ወስብሓት ለእግዚአብሔር፣
ወለወላዲቱ ድንግል፣
ወለመስቀሉ ክቡር።





አባ ሰይፊ ከገዳመ ጣማፍ በሰጊድ ላይ ሳሉ

ከዚህ ቀደም የታተሙ መጻሕፍት፦

፩. የሰማዕቱ ቅዱስ ሚናስ (ማር ሚና) ገድልና የፓትርያርክ ቂርኮስ ፯ኛ የሕይወት ታሪክ፣
፪. ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ፣
፫. ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፪ኛ መጽሐፍ፣
፬. የዋሁ ነቢይ ዮናስ፣
፭. ዘይት እፍካቂዋ ሥዕል ማርያም።
፮. ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፫ኛ መጽሐፍ፣
፯. ዝክረ ቅዱሳን ዘተዋሕዶ ፬ኛ መጽሐፍ፣

ቸር አምላካችን ዕድሜና ጤና ሰጥቶ፥ ቀጣዩን መጽሐፍ ከማንበብ ያብቃን። አሜን።